ቁጥር ሕ/ሥ/ጉ/00/08

ቀን ህዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም (21/11/08)

የርእሰ አድባራት ለገደን ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን
የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት

ለገደን

ጉዳዩ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ ውሳኔን ስለመላክ

ጥቅምት 28 ቀን 2001 (07/11/08) የዋለው የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ በ14/09/08 የተካሄደውን ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ አፈጻጸምና የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ በመሪጌታ መርሐጽድቅ ቀናው ላይ ያቀረበውን ክስና ውሳኔን በሚመለከት ያሳለፈውን 4 ገጽ የውሳኔ ቃለጉባኤ እና 3 ገጽ አባሪ ደብዳቤዎች በዚሁ መሸኛ ደብዳቤ አያይዘን የላክ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለሁ።

እግዚአብሔር አገልግሎታችንን ይባርክ!!

ልዑል ሚካኤል መኮንን
የጉባኤው ጊዜያዊ ሰብሳቢ

ግልባጭ
ለሰበካ ጉባኤ
ለቁጥጥር ኮሚቴ
ለሕንፃ ልማት ኮሚቴ
ለሰንበት ት/ቤት አመራር ኮሚቴ

ለሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ እንዲቀርብና ጉዳዩ ደረጃውን ጠብቆ በዳኝነት እንዲታይ ይህ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ አጥብቆ ይጠይቃል።

በዚህ ሕጋዊ መንገድ ባይፈጸም ቀርቶ ተከሳሹ ያለዳኝነትና ያለአግባብ ተበድያለሁ ብለው ለሚጠይቁት ሕጋዊ እርምጃም ሆነ ሕግን በመጣስና ሕግን ተከትሎ ባለመሥራት የሚነሣት በጠቅላላው በቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን አንድነትና ሰላም ላይ ለሚፈጠረው ችግር የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ተጠያቂ መሆኑን የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ አጥብቆ ያሳውቃል። ከዚህም ሌላ በዚህና ከዚህ በፊት በሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ በተሰጡት የሕግ ምክርና ማሳሰቢያዎች መሠረት የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ከዚህ በፊት የታዩትን ስህተቶች በማረም በቤተክርስቲያናችን የምንመራበትን ሕግ ተከትሎ የሚያስተዳድር ካልሆነ የሕግ አስከባሪ መኖሩ ዋጋ ስለሌለው ይህ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሕጉንና ሥርዓቱን ለማስከበርና በቤተክርስቲያናችን ግንዛቤና ንቃረት አጠባበቅ ላይ ሀሚት እንዲኖር መደረግ የሰበካን በሚመለከት ቁጥር ያደረገውን ጥረትና ፤ እንዲሁም የገጠሙትንና የታዩትን ችግሮች በዝርዝር ለጠቅላላው ጉባኤ አባላት አሳውቆ ሃላፊነቱን እንደሚያስረክብ በአንድ ድምጽ ተስማምቶ የሰሉቱ ጉባኤ ተፈጽሞዋል። የጉባኤውም ውሳኔ ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤና ለሌሎቹም ማወቅ ለሚገባቸው የኮሚቴና የካህናት ጉባኤ አባላት እንዲላክ ተስማምተዋል።